ረመዳን ሙባረክ

بسم الله الرحمن الرحيم

# በአውሮፓ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ኔትወርክ
# የረመዳን 1428 መልዕክት

*የተከበራችሁ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች! አስቀድመን እንኳን ለተከበረው የረመዳን ወር አላህ በሰላም አደረሰን እንላለን። ረመዳን ሙባረክ።*

*ውድ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች!*

ባሳለፍነው አመት በርካታ ሙስሊሙን ማዕከል ያደረጉ ክስተቶች በሀገራችን ተከስተዋል፤ የሙስሊሙን ጉዳይ የዳሰሱ ክንዋኔዎችም ተደርገዋል። በሀገር ውስጥ እና በውጭ ያሉ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች የሀገሪቱ ህገ-መንግስት ያጎናጸፋቸውን የሀይማኖት እና የዜግነት መብታቸውን ለማስከበር፣ በሀገራቸው ጉዳይ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ፣ ባህላቸውን ለማጠናከር የሚያስችሉ የተለያዩ እና የተቀናጁ እንቅስቃሴዎችን አድርገዋል። ከእነዚህ እና መሰል እንቅስቃሴዎች መካከል በአመቱ አጋማሽ ላይ ሙስሊሙ ህብረተሰብ ባሉበት ችግሮች ዙሪያ ከመንግስት ባለስልጣናት ጋር ለመወያየት ወደ ኢትዮጵያ የሄደው የዲያስፖራው ኢትዮጵያዊያን ሙስሊም የልዑካን ቡድን ለአብነት የሚጠቀስ ነው። ኔትወርካችንም ለዚህ በታሪካችን የመጀመሪያ በሆነው ታሪካዊ እርምጃ ከጽንሰ ሀሳቡ ጀምሮ ተሳታፊ በመሆን ለስኬቱም የራሱን አስተዋጽዖ አድርጓል፤ እያደረገም ይገኛል።

የአንድ ህብረተሰብ ታሪክ በተለያዩ ወቅቶች የኖረና የሚኖር ትውልድ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች የሚከሰት ሲሆን የታሪክ ዘመኑ በጎ ገጽታና ጉድለትም የሚለካው በየጊዜው የነበረው ትውልድ በሚወስዳቸው ወይም በማይወስዳቸው እርምጃዎች ጥንካሬ እና ድክመት መጠን ነው። ይህም በመሆኑ ዛሬ የምናደርጋቸው ተግባራት፣ የምንወስዳቸው እርምጃዎችና የምንይዛቸው አቋሞች የነገው ታሪካችን አካል በመሆን በመጭው ትውልድ ዘንድ ተጠያቂዎች ያደርገናል። ከላይ ለአብነት የጠቀስነው ታሪካዊ እርምጃም፣ በቀጣይ ለገቢራዊነቱ የምናደርገው ማንኛውም እንቅስቃሴም በነገው ታሪካችን ውስጥ የራሱን ልዩ ቦታ የሚይዝ ይሆናል።

የልዑካኑ ጉዞ ያስመዘገባቸው መልካም ነጥቦች በርካታ ቢሆኑም ሙስሊሙ ህብረተሰብ አሉብኝ በሚላቸው ችግሮች ላይ የጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ ከአገሪቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር መግባባት ላይ መድረስ በቀድሚያ የሚጠቀስ ነው። ሆኖም ግን ችግርን ማሳወቅ እና ለውይይት በቀርቡ ነጥቦች ላይም መግባባት መቻል በራሱ ግብ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል አይደለም። የሙስሊም ህብረተሰብ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ያገኙ ዘንድ መንግስትም ሆነ ሙስሊሙ ህብረተሰብ ሊወጧቸው የሚገባ የየራሳቸው ሃላፊነቶች አሉባቸው።

---

ረመዳን ሙባረክ

ሙስሊሙ ህብረተሰብ መብቱን ለማስከበር ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል። ለመንግስት የቀረቡ ጥያቄዎችም እልባት እንዲያገኙ፤ ቀጥሎም የሚገኙ መፍትሄዎች ዘለቄታ እንዲኖራቸው የሙስሊሙ ህብረተሰብ ተሳትፎና ያልተቆጠበ ጥረት ያስፈልጋል። በተለይም በዚህ ከመንግስት አካላት ጋር ውይይት ያካሄደው የበድር አለም አቀፍ የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ፌደሬሽን ለተፈጻሚነቱ ይረዳ ዘንድ በአለም አቀፍ ደረጃ ያቋቋማቸውን ንዑስ ኮሚቴዎች ለስራ ማንቀሳቀስ፤ የተሰጡትን ሀላፊነት የት እንዳደረሱ መከታተል እና ውጤቱንም ለህዝብ ማሳወቅ ይጠበቅበታል። እነዚህ ኮሚቴዎችም የተጣለባቸውን ሀላፊነት ለመወጣት ጠንክረው መስራት አለባቸው። ከሰፊው ሙስሊም ህብረተሰብ ጋርም የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር እና የመገናኛ መስመሮችን በመዘርጋት በሀገርም ሆነ በውጭ የሚንቀሳቀሱበትን መንገድም መቀየስ አለባቸው።

የሙስሊሙ መሰረታዊ ድሞክራሲያዊ መብት ከህገ መንግስቱ ውጭ ተሸርሽሮ የሚገኝባቸው ሁኔታዎች በርካታ ናቸው። ሙስሊሙ ህብረተሰብ እራሱን የማደራጀት መብቱ ከመገደቡ እና የበላይ ምክር ቤቱንም በሚፈልገው መልኩ ማደራጀት ካለመቻሉ ጀምሮ በአክሱም ሙስሊሞች የዜግነት እና የሰብዓዊ መብቶቻቸውን በእጅጉ ተነፍገው ይገኛሉ። የዜጎች በህገ መንግስቱ የሰፈሩ መብቶች ተግባር ላይ ሳይውሉ የድሞክራሲያዊ ስርዓትን ማዳበር፣ በኢኮኖሚው እና በማህበራዊ ኑሮ ዘርፍም እድገትን ማስመዝገብ አይቻልም። ስለሰላም እና እኩልነትም መናገር አስቸጋሪ ይሆናል። መንግስት እነዚህን መሰረታዊ የዜጎች መብቶች ገቢራዊነት የመከታተል እና የማስፈጸም ሀላፊነት አለበት እና ይታሰብበት እንላለን። ከዚህ በተጨማሪ መንግስት የቀረቡለት የሙስሊሙ ጥያቄዎች ምላሽ ያገኙ ዘንድ የገባውን ቃል በአፋጣኝ ወደ ተግባር መለወጥ ይጠበቅበታል።

*ውድ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች!*

በዚህ በየአመቱ በናፍቆት በምንጠብቀው ረመዳን ወር ከምናደርጋቸው የኢባዳዎች ተግባራት ጎን ለጎን የሙስሊሙን አጠቃላይ ሁኔታ በመከታተል የእውቀትና የገንዘብ ሃይላችንን ለህብረተሰባችን እድገት እንድናውል ጥሪ እናደርጋለን። ለተከበረው ወርም ልዩ ትኩረት በመስጠት ከመቸውም በላይ በተጠናከረ የኢባዳ ስራ ላይ እንበርታ፣ እንበረታታ። አላህንም በብዙ በማውሳት በእዝነቱ እና ርህራሄው ለሀገራችን እና ለህዝባችን ሰላምን፣ እድገትን፣ መግባባትን እና መቻቻልን እንድሰጥልን በጽኑው እንማጸነው።

የዲን ፍቅር መለኪያው ተግባር ነውና በእምነታችንም በኩል ይሁን በህዝባችን እና ሀገራችን ዘንድ ያለብንን ታሪካዊ አደራ እንወጣ። አላህ ይርዳን።

**ሴፕቴምበር** 13፣ 2007


**በአውሮፓ የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ኔትወርክ።**
http://www.ethiopianmuslims.net
neme@ethiopianmuslims.net